QuickNotes ዜና መጽሔት መድብል 1 ኦክቶበር 2014

**ሪፖርት ካርዶች፡- የወላጅ መመርያ**

የልጅዎን የ2014-2015 ሪፖርት ካርድ በሚከተሉት ቀኖች ይመልከቱ፡- ኖቨ. 12፣ ጃን. 29፣ ኤፕረል 14 እና ጁን 23።

ወላጆች፣ የልጃችሁ የመጀመርያ ሪፖርት ካርድ ቤት የሚመጣው ሮብ፣ ኖቨ. 12 ነው። ሪፖርት ካርዶች በሚከተሉት ቀኖችም ወደ ቤት ይላካሉ፡-

- ጃኑዋሪ 29
- ኤፕረል 9
- ጁን 23 (ሪፖርት ካርዶች በፖስታ ይላካሉ)

ከK–5 የሚገኙ ተማሪዎች በመመዘኛ-የተመሰረተ (standards-based) ሪፖርት ካርድ መቀበል ይቀጥላሉ፣ ይህም ስለ ልጅዎ አፈፃፀምና ግስጋሴ ተጨማሪ መረጃዎች ይሰጣል።

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ወላጆች አመቱን በሙሉ የልጃቸውን ማርኮች በEdline መከታተል ይችላሉ። ይህ በድር-የተመሰረተ የመገናኛ መሳርያ የመካከለኛና የከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ወላጆች የልጆቻቸውን ማርኮችና የስራ ትእዛዞች/የቤት ስራዎች ለመቆጣጠርና ወደ መምህራን ኢሜይል ለማድረግ ያስችሏቸዋል። በዚህ የትምህርት አመት በሙሉ፣ የተወሰኑ የኤሌሜንታሪ፣ መካከለኛ፣ እና ከፍተኛ ት/ቤቶች አዲሱን *myMCPS ስርአት ሙከራ ያካሂዳሉ።* ይህ ስርአት የመማርያ ክፍል እቅድ የማውጣት ገፅታ፣ ማስታወቂያ ስርጭቶች፣ እና በተጨማሪ ለክፍል ስራዎችና ማርኮች መዳረሻ በተጨማሪ ይሰጣል። የልጅዎ ት/ቤት፣ በዘለቄታው ለሁሉም የMCPS ወላጆች ክፍት የሚሆነውን አዲሱን ስርአት መገልገል ሲጀምር፣ ወደ ጣብያው አገናኝን ጨምሮ፣ ይበልጥ ዝርዝር መረጃዎች ይገኛሉ።

ስለMCPS የውጤት አሰጣጥና ዘገባ አፈፃፀም ተጨማሪ መረጃ ፍላጎት ወይም ስለ በመመዘኛ-የተመሰረቱ ሪፖርት ካርዶች ጥያቄዎች አላችሁን? የየማርክ መስጫ እና ዘገባ ድርጣብያን ይጎብኙ።

**Superintendent Starrን ለ2014 አመታዊ ዘገባ ይቀላቀሉት**

ኖቨ. 11 ከእኛ ጋር መቀላቀልዎን ያስታውቁን። እባክዎን መልሱን በwww.mcpsstateoftheschools.org ይስጡ።

Superintendent Joshua Starr ሶስተኛውን አመታዊ የት/ቤቶች ይዞታ ዲስኩር በስትራትሙር የሙዚቃ ማእከል ማክሰኞ፣ ኖቨ. 11 2014 ይሰጣል። Dr. Starr ተማሪዎቻችንን ለወደፊታቸው ስኬት

እንዴት እንደምናዘጋጃቸው ራእዩን ያካፍላል። ክውነቱ ለህዝብ ነፃና ክፍት ነው። ከቀላል ቁርስ እና በሙዚቃ ማእከሉ በሞላ በMCPS ተማሪዎች የሚከናወኑ ትርእይቶችና የስነ ጥበብ ሰራዎች የማየት እድል ያለው በአል በ7:30 a.m. ይጀምራል። በ8:30 a.m፣ Dr. Starr የት/ቤቶች ይዘት ዲስኩሩን ያቀርባል። ክውነቱ በ9:30 a.m. እንደሚያልቅ ይጠበቃል። የውጭ ቋንቋ ትርጉምና የምልክት ቋንቋ ይኖራል።

እነደምናይዎት ተስፋ አለን። እባክዎን እስክ ኖቭ. 3 መልሱን በ[www.mcpsstateoftheschools.org](http://www.mcpsstateoftheschools.org) ይስጡ።

[የትምህርት ቤቶች ይዘት]()

**ለ2014 ት/ቤትን መሰረት ባደረጉ የፍሉ ክሊኒኮች ክትባት ይመዝገቡ**

የMontgomery County የጤና እና የህዝባዊ አገልግሎቶች መምርያ ነፃ በአፍንጫ የሚረጭ የፍሉ ክትባት ክሊኒኮች በተለያዩ የMCPS ት/ቤቶች በኖቨምበር ወር ያካሂዳል።

የ2014 የፍሉ ወራት ደርሶብናል። ጤናማ ለመሆንና ፍሉን ለመከላከል እርስዎና ልጅዎ መውሰድ የምትችሏቸው ቀላል እርምጃዎች አሉ። ያም በየአመቱ የፍሉ ክትባት መውሰድን ያካትታል።

የMontgomery County የጤናና የስብአዊ አገልገሎቶች መምርያ ነፃ በአፍንጫ የሚረጭ የፍሉ ክትባት ክሊኒኮች (FluMist) በተለያዩ የMCPS ት/ቤቶች ለሚገኙ ልጆች በኦክቶበርና በኖቨምበር ያካሂዳል።

አርብ፣ ኦክቶ. 31፣ ካውንቲው የፍሉ ክሊኒኮች በJohn F. Kennedy፣ Richard Montgomery እና በSeneca Valley ከፍተኛ ት/ቤቶች ያካሂዳል። የዚያን እለት የመምህራን የባለሙያ ቀን ስለሆነ ትምህርት አይኖርም። ህክምናዎቹ ለማንኛውም በትምህርት እድሜ ውስጥ ለሚገኝ ልጅ ክፍት ይሆናሉ።

ሁሉም የMCPS ኤሌሜንታሪ ትም/ቤቶች ሰኞ ኖቨምበር 10 ወይም ማክሰኞ ኖቨምበር 11፣ ተማሪዎች በቅድሚያ ከተለቀቁ በኋላ፣ የፍሉ ህክምና ያስተናግዳሉ። ተጨማሪ መረጃ ከልጅዎ ትም/ቤት ወደ መኖርያ ቤት ይላካል።

ሁሉም ክሊኒኮች ነፃ ናቸው፣ ነገር ግን የክትባት አቅርቦቶች የተወሰኑ ስለሆነ ምዝገባ ያስፈልጋል። ለተጨማሪ መረጃዎች፣ [የMontgomery County የጤናና የስብአዊ አገልገሎቶች መምርያ ድርጣብያ]() ይጎብኙ።

የፍሉን እና የሌሎች ወቅታዊ በሽታዎች ስርጭትን ለመከላከል እርስዎና ቤተሰብዎ ልትወስዷቸው የምትችሉ ተጨማሪ እርምጃዎች እነዚህ ናቸው፡-

1. እጆቻችሁን አዘውትሮ በሳሙናና በውሃ መታጠብ፣ በተለይ ከሳላችሁ ወይም ካስነጠሳችሁ በኋላ፣ ወይም አልኮል ባዘለ የእጅ ማጽጃ መጠቀም። MCPS-ያፀደቃቸው የእጅ መፀዳጃ መስጫዎች

በት/ቤቱ በሞላ በተለያዩ ስፍራዎች ይገኛሉ (ለምሳሌ በምግብ ቤት (cafeteria) በሁለገብ ክፍል (all-purpose room)፣ ዋናው ፅ/ቤት አጠገብ)።
2. ሲያስላችሁ ወይም ሲያስነጥሳችሁ፣ አፍንጫችሁንና አፋችሁን በእጅጌ ወይም በመሃረም/ቲሹ ሸፍኑ እና መሃረሙን/ቲሹውን ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጣሉት።
3. በተላላፊ የመለከፍ እድልን ለመቀነስ አይኖቻችሁን፣ አፍንጫ ወይም አፋችሁን ከመንካት ተቆጠቡ።
4. ትኩሳት፣ ሳል፣ ማስነጠስ፣ ፈሳሽ ንፍጥ፣ የራስ ምታት እና የአካል ህመም የመሳሰሉ ምልክቶች ከተሰሙ ከስራ ወይም ከት/ቤት ቀርቶ ቤት መዋል።
5. ስለ ልጅዎ ጤና ቅር ከተሰኙ፣ እባክዎ ሃኪምዎን ወድያውኑ ያግኙ ወይም፣ አስቸኳይ ከሆነ፣ 911 ይደውሉ።

ተጨማሪ የፍሉ መከላከያ መረጃዎች በሚከተሉት ድርጣብያዎች ይገኛሉ፡-

MCPS http://www.montgomeryschoolsmd.org/emergency/flu/index.aspx/
Centers for Disease Control (የበሽታ መቆጣጠርያ ማእከሎች)
http://www.cdc.gov/flu/protect/preventing.htm
Montgomery County http://www.montgomerycountymd.gov/resident/flu.html

**አዲሱን የቦርድ ብሎግ አንብቡ**

**በአዲሱ የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ብሎግ ይሳተፉ እና መረጃ ይኑርዎት**

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ብሎግ እየፃፈ ነው! አዲሱ የቦርድ ብሎግ አስፈላጊ ዜናዎችና መረጃዎች፣ የቦርድ ስብሰባ ማጠቃለያዎች፣ እና ማህበረሰቡ በቦርዱ ስራ እንዲሳተፍ እድሎች ይሰጣሉ። ብሎጉን በትምህርት ቦርድ ድርጣብያ ማግኘት ይችላሉ። ለአዲስ መልእክቶችና መረጃዎች በየወቅቱ ተከታተሉ።

**የትምህርት ቦርድ ብሎግ**

**መቆጣጠርያ ዝርዝር፡- ኮንሶርሺያ እና ማመልከቻ-ብቻ ፕሮግራሞች**

MCPS ለሁሉም ተማሪዎች በሁሉም የክፍል ደረጃዎች የተለያዩ የበለፀጉ የአካዴሚ ፕሮግራሞች ያቀርባል። ይህ የመቆጣጠርያ ዝርዝር (checklist) በ*Choice* (ምርጫ) ሂደት እና ማመልከቻ-ብቻ ፕሮግራሞች ትኩረት ለሚያደርጉ ወላጆች የተወሰኑ አስፈላጊ መረጃዎች ያቀርባል።

MCPS ጠንካራ፣ ትኩረት-ጠያቂ እና የበለፀጉ የአካዴሚ ፕሮግራሞች በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ለሚገኙ ተማሪዎች ያቀርባል። አንዳንድ ፕሮግራሞች ስፖንሰር ለሚያደርጋቸው ትም/ቤት ተማሪዎች ብቻ ክፍት ናቸው፣ ሌሎቹ ደግሞ በካውንቲው ለሚገኙ ለሁሉም ተማሪዎች ክፍት ናቸው። እነዚህ ፕሮግራሞች የተለያዩ የመግቢያ መስፈርቶችና የማመልከቻ ሂደቶች አሏቸው። ይህ የመቆጣጠርያ ዝርዝር (checklist)

ለልጃቸው/ለልጆቻቸው *Choice (ምርጫ)* ሂደት እና ማመልከቻ -ብቻ ፕሮግራሞች ፍላጎት ላላቸው ወላጆች የተወሰኑ ጠቃሚ መረጃዎች ይሰጣል።

- ✓ ስለ Choice ሂደትና ማመልከቻ -ብቻ ፕሮግራሞች ተጨማሪ መረጃ የሚከተሉትን ድር ጣቢያዎች ጎብኙ፡-

  North East ኮንሶርሺየም
  Downcounty ኮንሶርሺየም
  Middle School Magnet ኮንሶርሺየም
  *ማመልከቻ-ብቻ ፕሮግራሞች*

- ✓ በክፍት ስብሰባዎች (open houses) በመገኘት በዚህ ወር ስለ *Choice* ፕሮግራሞች በNortheast ኮንሰርሽም (NEC) እና Downcounty ኮንሰርሽም (DCC) ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና በMiddle School Magnet ኮንሰርሽም (MSMC) መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተከታተሉ። ስለ ማመልከቻ-ብቻ ፕሮግራሞች ይበልጥ ለመማር የመረጃ ስብሰባዎች በተለያዩ የኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች በሚገኙ የክፍተኛ ተሰጥኦ ማእከሎች (Centers for the Highly Gifted) እና በRoberto Clemente፣ Eastern እና Takoma Park መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ እና Montgomery Blair፣ Richard Montgomery እና Poolesville ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መከታተል ትችላላችሁ።
  *ቀኖችንና ቦታዎችን ይያዙ*

- ✓ የልጅዎን ፍላጎት እጅጉን የሚስማማ ፕሮግራም ላይ ከወሰኑ በኋላ፣ ማመልከቻውን ከአርብ ኖቨምበር 7 የግዜ ገደብ በፊት ያስገቡ። የኮንሶርሺያ ትም/ቤቶች ወላጆች የ*Choice* ቅፆች በፖስታ ኦክቶበር አጋማሽ ላይ ያገኛሉ።

- ✓ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች? የSpecial Programs (ልዩ ፕሮግራሞች) ድርጣብያ ይጎብኙ ወይም 301-592-2040 ይደውሉ።

**ወደ Montgomery አለም በአል ይምጡ**

የMontgomery County እና የWashington, D.C. አካባቢ የበለጸገ የባህል ቅርስ Westfield Wheaton Mall በሚገኘው የMontgomery አለም በአል ኦክቶ. 19 በመገኘት አክብሩ።

የ Montgomery አለም በአል የMontgomery County እና የWashington, D.C. አካባቢ የበለጸገ ባህላዊ ቅርሶችን ያከብራል ያሳያልም። በአሉ በWestfield Wheaton Plaza Mall የመኪና ማቆሚያ ስፍራ (ሜትሮ አጠገብ) እሁድ፣ ኦክቶ. 19፣ ከቀትር እስከ 5 p.m. ይካሄዳል

በMontgomery ገንዘብ (Fund) የተደገፈና በKID Museum የተዘጋጀ ሆኖ፣ በአሉ አለም አቀፍ መንደር፣ በዋና ባለሙያ የባህል ምግብ ዝግጅት ትርእይት የታጀበ አለም አቀፍ ባልትና፣ የእጅ ስራ ሽያጭ፣ የባህሎች ሰልፍ (Parade of Cultures)፣ ሁለት የባህላዊ ዳንስና ሙዚቃ የመድረክ

አቅርቦቶች፣ የአገልግሎቶች ግንኙነቶች፣ ባህላዊ ኪነጥበባት፣ እና ለቤተሰብ በሞላ አሳታፊ የእርስበርስ እንቅስቃሴዎች ያካትታል።

ለተጨማሪ መረጃዎች፣ www.worldofmontgomery.comን ጎብኙ።

## Trades Foundation የመኪና ስጦታዎች ይፈልጋል

ካሁን ወድያ የማያስፈልግዎ መኪና እና ሊሰጡት የምትፈልጉ መኪና አለዎት ወይ? የMontgomery County Students Automotive Trades Foundation (የተማሪዎች የመኪና ጥገና ድርጅት) (ATF) የመኪና ስጦታዎች እየፈለገ ነው።

የMontgomery County Students Automotive Trades Foundation (የተማሪዎች የመኪና ጥገና ድርጅት) (ATF) የመኪናዎች ስጦታ እየፈለገ ነው። ስጦታዎ 350 የሚደርሱ የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ተማሪዎችን መኪናዎችን መመርመር፣ መጠገንና ማደስ ለመማር ሊያግዛቸው ይችላል። ATF ለተማሪዎች የእንክብካቤ፣ የጥገና፣ የሽያጭና የግብይት ተግባራዊ ስልጠና በመስጠት የመኪና ምህንድስና (automotive) ትምህርት የሚሰጥ በጎ አድራጎት ነው። መኪኖቹ በDamascus፣ Gaithersburg፣ Seneca Valley ወይም በThomas Edison ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሚገኙ የመኪና ምህንድስና ፕሮግራሞች ይበረከታሉ። ሰጭዎች የታክስ ቅናሽ የማግኘት ብቃት አላቸው።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የATF ድር ጣብያ ይጎብኙ እና Donate Your Car የሚለውን ትር ጠቅ አድርጉ። ወይም፣ Mike Snyder (ማይክ ስናይደር)ን በ301-929-2164 ተገናኙ።

## MCPS በዜናዎች

ስለ MCPS ወቅታዊ የጋዜጣ መግለጫዎች፣ የዜና ርእሶች፣ የቪድዮ ትረካዎች ይከታተሉ።

ጥቂት ትርፍ ደቂቃዎች አለዎት ወይ? እንግዲያስ ስለMCPS ወቅታዊ ርእሰ አንቀፆች፣ ቪድዮዎች እና የጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይከታተሉ።

***ቪድዮዎች***
MCPS የወደ ት/ቤት የእግር ጉዞ ያከብራል
NAACP የወላጆች ምክርቤት የመጀመርያውን (Kick-Off) ስብሰባ ያካሂዳል
የ2014 ተመራቂ ክፍል በSAT ልቆ ይገኛል

***MCPS በዜናዎች***
ተማሪዎች በወደ ት/ቤት የእግር ጉዞ ይሳተፋሉ
Luxmanor Elementary ገንዘቡን ወስዶ ይጓዛል
የMCPS ተመራቂዎች በስቴትና በአገር ደርጃ በSAT ልቀው ይገኛሉ
የSAT ውጤቶች እድገት አሳዩ፣ ከሂስፓኒኮችና አፍሪካ አሜሪካኖች አወንታዊ ግኝት ጋር
በMontgomery የሂስፓኒኮች የረጅም ጊዜ የምዝገባ እድገት

Cashell Elementary - National Blue Ribbon School ተብሎ ተሰየመ

*ጋዜጣዊ መግለጫዎች*

Cashell Elementary - የ2014 National Blue Ribbon School ተብሎ ተሰየመ
የSAT ውጤቶች ለMCPS 2014 ተመራቂዎች እድገት አሳዩ
የትምህርት ቦርድ ስቴቱን ለአዲስ ፈተናዎች የምረቃ ተፈላጊነት እንዲያዘገይ ጠየቀ

**ታላላቅ ት/ቤቶች፣ ተማሪዎች እና ሰራተኞች**

Cashell Elementary የ2014 National Blue Ribbon School ተብሎ በዩ.ኤስ. የትምህርት መምርያ ተመረጠ። መንገዱ፣ Cougars!

በቅርብ ጊዜ የWheel of Fortune የ$1 ሚልዮን አሸናፊ የሆነችውን የTakoma Park Middle School የላቀች መምህር ሳራ ማንቸስተርን (Sarah Manchester) ያግኙ።